የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፵፫
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፱ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

18th Year No. 43
ADDIS ABABA 6th July, 2012

<u>ማውጫ</u>

አዋጅ ቁጥር ፯፻፶/፪ሺ፬ ዓ.ም

በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በግብፅ አረብ ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል የተደረገው ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ …… **ገጽ ፮ሺ፫፻፷፬**

**<u>CONTENTS</u>**

**Proclamation No.750/2012**

Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Arab Republic of Egypt for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income Ratification Proclamation. ... Page 6364

## አዋጅ ቁጥር ፯፻፶/፪ሺ፬

**<u>በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በግብፅ አረብ ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል የተደረገውን ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በግብፅ አረብ ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል የሚያስችል ስምምነት እ.አ.አ. ሴፕቴምበር ፲፭ ቀን ፪ሺ፲፩ በካይሮ ከተማ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፲፬ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION No. 750/2012.

**<u>A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE ARAB REPUBLIC OF EGYPT FOR THE AVOIDANCE OF DOUBLE TAXATION AND THE PREVENTION OF FISCAL EVASION WITH RESPECT TO TAXES ON INCOME</u>**

WHEREAS, Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Arab Republic of Egypt for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect Taxes on Income was signed on 15th September 2011, in Cairo;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Agreement at its session held on the 21st day of June 2012;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 sub-article (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በግብፅ አረብ ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል የተደረገው ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፯፻፶ /፪ሺ፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## ፪. የስምምነቱ መፅደቅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በግብፅ አረብ ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል እ.አ.አ ሴፕቴምበር ፲፭ ቀን ፪ሺ፲፩ በካይሮ ከተማ የተፈረመው በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል የሚያስችለው ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

## ፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር አግባብ ካላቸው የመንግስት አካላት ጋር በመተባበር ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

## ፬. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ ፳፱ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም**

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ

ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Arab Republic of Egypt for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income Ratification Proclamation No.750/2012".

## 2. Ratification of the Agreement

The Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Arab Republic of Egypt for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income signed on 15th September 2011is hereby ratified.

## 3. Power of the Ministry of Finance and Economic Development

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to implement the Agreement in cooperation with the concerned government organs.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 6th day of July, 2012.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**